## በኢ.ፌ.ዲ.ሪ የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ

# ስደተኞች ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ የሚንቀሳቀሱበትና የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 431/2013

## መግቢያ

ኢትዮጵያ ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ስደተኞችን ተቀብላ ባፀደቀቻቸዉ የስደተኞችን ጉዳይ በሚገዙ አለም ዓቀፍና አህጉር ዓቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም በአለም አቀፍ መርሆች ጋር ተጣጥሞ እንደ አዲስ በወጣው የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 መሰረት ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ከለላና ሰብዓዊ ድጋፍ እየሰጠች ትገኛለች፡፡

በአዲስ የጸደቀው የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ለውጪ አገር ዜጎች በአጠቃላይ በተመሳሳይ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆኑ ህጎች እንደተጠበቁ ሆነው በመረጡት የአገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት ነፃነት አላቸው፡፡በተጨማሪም ይህንን መሠረታዊ መብት ለማስተግበር የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ስደተኞቹ ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎቹ የሚኖሩባቸውን ቦታዎችና አካባቢዎች ለማመቻቸት እንዲሁም ከቦታ ቦታ የመዘዋወር መብታቸውን እንዲጠቀሙ ለማስቻል ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

በዚህ መሰረት ስደተኞች ከተረጂነት ተላቀዉ ራሳቸዉን የሚችሉበትና ዘላቂ መፍትሔ የሚያገኙበትን እድል ለማስፋት ከሚከናወኑ ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴዎች መካከል በኤጀንሲዉ ተግባራዊ እየተደረገ የሚገኘዉ ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ የሚንቀሳቀሱበት፣ በመደበኛነት መኖር የሚያስችላቸዉ ሁኔታ (Out of Camp Policy /OCP/) እንዲሁም ድጋፍ እያገኙ በከተማ ስደተኝነት የሚኖሩበት (Urban Assisted) ሁኔታዎች ይገኙበታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ስደተኞች በካምፕ ብቻ ታጥረው መኖር ሳይጠበቅባቸው ሕጋዊ አሠራርን ተከትለው በአገሪቷ ውስጥ በሚፈጠሩ የተለያዩ የሥራ እድሎችን ለመጠቀምና ሕይወታቸውን ለመቀየር ሲፈልጉ ከካምኘ ውጪ የመኖር እድል እንዲሰጣቸው በማሰብ ከዚህ ቀደም የነበረው ስደተኞችን ከካምኘ ውጪ እንዲኖሩ የሚፈቅደው አሠራር እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ወጥ በሆነና ከስደተኛ ኮንቬንሽንና፣ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅና ተዛማጅ አለማ አቀፍ መርሆዎች ጋር በተጣጣ መመልከ የአሰራርን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. የመመሪያው አስፈላጊነት

ስደተኞች በካምፕ ብቻ ታጥረው መኖር ሳይጠበቅባቸው ህጋዊ አሰራርን ተከትለው የስደተኞች አዋጅ ቁጥር 1110/2011 በሚፈቅደው መሰረት በአገሪቱ ውስጥ በሚፈጠሩ የተለያዩ የስራ እድሎች ለመጠቀም እንዲችሉ ከካምፕ ውጪ የመኖር ዕድል አግኝተውና ከተረጂነት ተላቅቀው ህይወታቸው እንዲቀየር በማሰብ ከዚህ ቀደም የነበረው ስደተኞችን ከካም ውጪ እንዲኖሩ የሚፈቅደው አሰራር ስርዓት እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡ በዚህም መሰረት ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎችን ወጥ በሆነና ከስደተኞች ኮንቬንሽንና ተዘማጅ አለማቀፍ መርሆችን ባጣጠመ መልኩ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

### 2. የአውጪው ባለሥልጣን

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ በስደተኞች ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 46(2) በተሰጠው ስልጣን መሠረት ስደተኞች ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ የሚንቀሳቀሱበትና የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመወሰን ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 3. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ስደተኞች ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ የሚንቀሳቀሱበትና የሚኖሩበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 431/2013  ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 4. ትርጉም

1. “አዋጅ” ማለት የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 1110/2011 ነው፡፡
2. “ኤጀንሲ” ማለት የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
3. “ስደተኛ” ማለት በስደተኞች አዋጅ ላይ የተሰጠውን ትርጓሜ የሚይዝ ሲሆን በልዩ ሁኔታ ካልተመለከተ በስተቀር ጥገኝነት ጠያቂንም ይጨምራል፡፡
4. “ስፖንሰር” ማለት የስደተኛውን ወይም ጥገኝነት ጠያቂውን ሙሉ ወጭ ሸፍኖ ከካምፕ ውጭ ለማኖር ኃላፊነት የሚወስድ ሰው ማለት ነው፡፡

5. “ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚሰጥ ፍቃድ” ማለት ስደተኛው ወይም ጥገኝነት ጠያቂው ሙሉ ወጪውን በራሱ ወይም በስፖንሰር ሽፍኖ ከስደተኛ መጠለያ ወይም የመኖሪያ ቦታ ውጭ በመረጠው ቦታ እንዲኖር ሲፈቀድለት ማለት ነው፡፡
6. “የይለፍ ፈቃድ” ማለት አንድ ስደተኛ ከመጠለያ ጣቢያው ወይም መደበኛ መኖሪያ ቦታው ውጭ ለተወሰነ ጊዜና ቦታ ለመንቀሳቀስ እንዲረዳው በኤጀንሲው የሚሰጠው የድጋፍ ወረቀት ነው፡፡
7. “ቤተሰብ” ማለት፤

   ሀ) የስደተኛው ባል ወይም ሚስት፣

   ለ) ከአስራ ስምንት አመት በታች የሆነ ያላገባ የስደተኛ ወይም የጥገኝነት ጠያቂ ልጅ እና

   ሐ) እርስ በእርስ ያላቸው ጥገኝነት ግምት ውስጥ በማስገባት ኤጀንሲው በሚያደርገው ማጣራት እንደ ቅርብ ቤተሰብ የቆጠረው ሰው ማለት ነው፡፡
8. በአዋጁ ትርጉም የተሰጣቸው ቃላትና ሃረጎች በዚህ መመሪያ ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡
9. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴትም ፆታ ያገለግላል፡፡

5. **መርሆዎች**

1. ይህ መመሪያ በዘር፣ በሃይማኖት፣ በዜግነት፣ በአንድ የህብረተሰብ ክፍል አባልነት፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ወይም በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች ልዩነት ሳይደረግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
2. ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት የመኖር ሁኔታ በአንድ ጊዜ ለሁሉም ስደተኞች ክፍት የሚደረግ ሳይሆን በስደተኞች መብት ጥበቃ ረገድ መንግስት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ያላቸዉን አቅም፣ የፕሮቴክሽን ምህዳር፣ የስደኛዉ እራሱን ችሎ የመኖር አቅም፣ እና ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶችን ባገናዘበ መልኩ በጊዜ ሂደት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

3. ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት የመኖር ሁኔታ ስደተኞች ከአካባቢዉ ማህበረሰብ ጋር ያላቸዉን መስተጋብር ግምት ዉስጥ ባስገባ መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

6. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ዕውቅና ባገኙ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎችና በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ተሳትፎ በሚኖራቸው ማንኛውም ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ስለመኖር

7. **ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ መኖርያ ፈቃድ ስለመስጠት**

1. በዚህ ክፍል አንቀጽ 8 የተዘረዘሩ ሁኔታዎችን የሚያሟላ ማንኛውም ስደተኛ ይህንን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2. የፍቃድ ወረቀቱን የሚሰጠው ስደተኛው ተመድቦ የሚኖርበት መጠለያ ጣቢያ ወይም ማስ/ጽ/ቤት ወይም በኤጀንሲዉ ዋና መ/ቤት ሲሆን በአዲስ አበባ ለሚኖር ስደተኛ የኤጀንሲው ዋናው መ/ቤት ብቻ ይሆናል፡፡

3. ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር ጥያቄ የሚያቀርብ ስደተኛ ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ የኑሮ ሁኔታ እንዲሁም ስለሚሰጡ አገልግሎቶች በኤጀንሲዉ የግንዛቤ ማስጨበጫ ገለጻ ይደረግለታል፡፡

4. ይህ መመሪያ ከመዉጣቱ በፊት በነበረው አሰራር መሰረት ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ እንዲኖሩ ፍቃድ ያገኙ ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ የመኖር ፍቃዳቸው እንደጸና የሚቆይ ሲሆን የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች በነዚህ ስደተኞች ላይ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

5. ይህ መመሪያ ተፈፃሚ ከሚሆኑበት ቀን በፊት ከተመደቡበት የስደተኛ መጠለያ ጣቢያ መደበኛ ባልሆነ መንገድ ወጥተዉ የሚኖሩ ስደተኞች በዚህ ክፍል አንቀጽ 8 የተዘረዘሩ መስፈርቶችን እንደሚያሟሉ ተቆጥሮ በአቅራቢያቸው በሚገኘው የኤጀንሲው የመጠለያ ጣብያ ወይም ጽ/ቤት በመገኘት እዉቅና ማግኘት ይችላሉ፡፡

8. **ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎች**

1. በመጠለያ ጣቢያ ውስጥ በመኖር ላይ የሚገኝ ስደተኛ፤

ሀ). ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችለዉን ወጪ መሸፈን እንደሚችል ማረጋገጥ ሲችል፤ ወይም

ለ). ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችለዉን ወጪ መሸፈን የሚችል ስፖንሰር ማቅረብ ሲችል፤ ወይም

ሐ). በስራ ላይ ባሉ ህጎች መሰረት በሕጋዊ ሥራ ላይ መሰማራት የሚያስችለው የስራ ፈቃድ ሲያገኝ፤ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ዉስጥ ለሦስት ወራት (90 ቀናት) እና ከዛ በላይ መቆየቱ ተረጋግጦ ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት የመኖር ፈቃድ ይሰጠዋል።

2. ከላይ የተጠቀሰው ቢኖርም የሚያሳድገው አሳዳጊ በፍርድ ቤት ያገኘ ወላጅ አልባ ህፃን፣ ወይም ከቤተሰብ የተለየ ህፃን፣ በሐኪም የተረጋገጠ በሽታ ያለበት ስደተኛ/ጥገኝነት ጠያቂ፤ ህፃናትን ለብቻዋ የምታሳድግ እናት፤ አዛውንት እንዲሁም አስቸኳይ የዉጪ ጉዞ ዝግጅት ያለበት ስደተኛ 90 ቀናትን በመጠለያ ጣቢያ መቆየት ሳያስፈልግ በመጠለያ ጣቢያው ወይም ምዝገባ ጣቢያዎች ፕሮቴክሽን ኦፊሰሮችና አስተባባሪዎች በጋራ በሚሰጥ አስተያየት መሰረት በልዩ ሁኔታ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል።

3. በከተማ ድጋፍ እያገኘ የሚኖር ስደተኛ የከተማ ስደተኝነት ሁኔታ በሚያበቃበት ጊዜ ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችሉትን መስፈርቶች ማሟላቱ ተረጋግጦ ወደ መጠለያ ጣቢያ ለመመለስ ሳይገደድ ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት የመኖር ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል።

9. **ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የማያስችሉ ሁኔታዎች**

ከፀጥታና ወንጀል ጋር በተያያዘ በመጣራት ሂደት ላይ ያለ ወይም ከተላላፊ በሽታ ጋር በተያያዘ ምክንያት ክልከላ የተደረገበት ስደተኛ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፍቃድ አይሰጠውም።

## 10. የቤተሰብ አንድነት

1. ማንኛውም ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት የመኖር ፈቃድ ያገኘ ስደተኛ የቤተሰብ አባል የሆነ ስደተኛ ፈቃድ ከተሰጠው ስደተኛ ጋር በአንድነት ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር ፈቃድ እንዲሰጠው መጠየቅና ፍቃዱን ማግኘት ይችላል፡፡

2. በንዑስ አንቀጽ  አንድ መሰረት ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር ፈቃድ ያገኘ ለአካለ መጠን  ያልደረሰ ስደተኛ ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ መኖር ከጀመረ በኋላ አካለ መጠን ቢደርስ ወደ መጠለያ ጣቢያ እንዲመለስ አይገደድም፡

## 11. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የሚሰጥ ፈቃድ የሚያረጋግጣቸው ጥቅሞች

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፍቃድ የተሰጠው ስደተኞች ለጸጥታና ደህንነት ሲባል ኤጀንሲዉ በዚህ ወይም በሌላ መመሪያ መሰረት ክልከላ ከተደረገባቸው አካባቢዎች በስተቀር በሁሉም የሃገሪቱ አካባቢዎች በነጻነት የመዘዋወር እና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት መብት ይኖራዋል፡፡

2. በሀገሪቱ ህግ መሰረት በመንግስታዊ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ እንዲሁም ሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶች ለስደተኛ የሚሰጡ መሰረታዊ የስደተኝነት ከለላና ሌሎች አገልግሎቶችን ለማግኘት ያስችላል፡፡

## 12. ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፈቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች ግዴታዎች

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፈቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች በአዋጁ የተመለከቱት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል፡፡

2. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፈቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች ከዓለም አቀፍ ድንበር ከ30 ኪ.ሜ በታች ቅርበት ባላቸው አካባቢዎች እንዲሁም ለጸጥታና ደህንነት ሲባል ኤጀንሲዉ በዚህ ወይም በሌላ መመሪያ መሰረት ክልከላ ባደረገባቸው አከባቢዎች መኖርም ሆነ መዘዋወር አይችሉም፡፡

3. በህገ-ወጥ ስራዎች እና ለህዝብ ሞራል ተፀራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ያለመሰማራት እና የሀገሪቱን ህጎች የማክበር ግዴታ አለባቸው፡፡

## 13. ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የጥያቄ የሚቀርበበት ሥነ-ሥርዓት

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚፈልግ ስደተኛ በተመዘገበበት የመጠለያ ጣቢያ በአካል ቀርቦ የተዘጋጀውን ቅጽ መሙላት አለበት።

2. ጥያቄ አቅራቢ ስደተኛው ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችለዉን የተሟላ ወጪ መሸፈን እንደሚችል፤ ወይም ወጪውን መሸፈን የሚችል ስፖንሰር እንዳለው፣ ወይንም ሕጋዊ የስራ ፈቃድ፣ ወይም ከመጠለያ ጣብያ ውጪ የሚኖር የቤተሰብ አባል መኖሩን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።

## 14. ማስረጃዎች

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ጥያቄ የሚያቀርብ ስደተኛ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የሚያስችለውን የተሟላ ወጪ በራሱ መሸፈን እንደሚችል ጥያቄውን ለሚያስተናግደው የኤጀንሲው ሠራተኛ ሁኔታውን በማስረዳት ማረጋገጥ ይችላል።

2. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚፈልግ ስደተኛ የሚያቀርበው ስፖንሰር ማንነቱን የሚገልፅ የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም የመኖሪያ ፍቃድ በማቅረብ አቅራቢያው በሚገኝ የኤጀንሲው ጽ/ቤት፤ ወይም ስደተኛው በሚገኝበት መጠለያ ጣቢያ፣ ማስ/ጽ/ቤት ወይም አዲስ አበባ ዋናው መ/ቤት በአካል በመቅረብ ስፖንሰር መሆን እንደሚችል የሚያረጋግጠዉን ቅጽ በመሙላት የሚመለከተው ስደተኛ ወደ ሚገኝኝበት መጠለያ ጣብያ ማስላክ ይጠበቅበታል።

3. ለስደተኛው ስፖንሰር የሚሆነው ሰው በውጪ ሀገር የሚኖር ከሆነ ስደተኛውን ስፖንሰር ማድረግ እንደሚፈልግና እንደሚችል ባንክ ስቴትመንት በቃለ-መሃላ የተደገፈ ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል።

4. ሥልጣን ከተሰጠው አካል ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ የሚያቀርብ ስደተኛ ስራ ላይ መቀጠሩን የሚያሳይ ማስረጃ እንዲያቀርብ አይገደድም።

5. ከመጠለያ ጣብያ ውጪ በመደበኛነት የሚኖር የቤተሰብ አባል አለኝ በሚል ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር ጥያቄ የሚያቀርብ ስደተኛ የተባለው ሰው ከመጠለያ ጣብያ

ውጪ መኖሩን እና ከእርሱ ጋር ያለዉን ዝምድና በሚያቀርበዉ ጥያቄ መሰረት ኤጀንሲዉ ከመረጃ ቋት ላይ ከሚገኝ ማስረጃ ሊያረጋግጥለት ይችላል፡፡

## 15. ይግባኝ

1. ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር አመልክቶ በሚወሰነው ዉሳኔ ላይ ቅሬታ ያለበት ስደተኛ በየደረጃዉ ለካምፕ አስተባባሪ፤ለማስተባበሪያ ፅ/ቤት ሃላፊ እና ለምክትል ዋና ዳይሬክተር በጽሁፍ  ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
2. ይግባኝ ሰሚዉ የበላይ ሃላፊ ቅሬታዉን ከሚመለከታቸዉ የስራ ክፍሎች ጋር በመሆን ከመረመረ በኋላ በ 5 የስራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔዉን ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
3. በበላይ ሃላፊዉ የሚሰጠዉ ዉሳኔ የመጨረሻ እና በድጋሚ ይግባኝ የማይጠየቅበት ይሆናል፡፡

## 16. የሁኔታዎች ለውጥ

በዚህ መመሪያ መሰረት ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር ፈቃድ ለማግኘት ያስቻለው ሁኔታ በማናቸውም ምክንያቶች ቢለወጥ ወደ መጠለያ ጣቢያው መመለስ ሳያስፈልገው ሌሎች ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ማሟላቱን በማሳየት በመደበኛነት መኖር መቀጠል ይችላል፡፡

## 17. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚሰጥ ፈቃድ የሚቆይበት ጊዜ እና እድሳት

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የሚሰጥ ፈቃድ የሚያገለግለው ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ብቻ ነው፡፡
2. ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር ፍቃድ ያገኘስደተኛ በዚህ አንቀጽ የተገለጸው ጊዜ ከማለቁ በፊት ፍቃዱን በወሰደበት መጠለያ ጣቢያ ወይም ማስ/ጽ/ቤት ወይም ዋናው መ/ቤት በአካል በመቅረብ ፍቃዱን ማሳደስ ይኖርበታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገገው ቢኖርም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት በተገለጸው ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ፍቃዱን ማሳደስ ያልቻለ ስደተኛ ምክንያቱን ለኤጀንሲው በማስረዳት ፍቃዱን ማሳደስ ይችላል።

## 18. ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት መኖርን የሚያረጋግጥ መታወቂያን ስለመተካት

ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት መኖርን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ከጠፋ ስደተኛው ይህንኑ ሁኔታ የሚያስረዳ ደብዳቤ ከሚኖርበት አከባቢ ፖሊስ ጣብያ በማጻፍ ወይም ከተበላሸ የተበላሸውን የመታወቂያውን ቅሪት በመያዝ አቅራቢያው ከሚገኝ የኤጀንሲው ጽ/ቤት በአካል በመቅረብ ምትክ መታወቂያ ማግኘት ይችላል።

## 19. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚሰጥ ፈቃድ የሚያበቃበት ሁኔታዎች

1. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የተሰጠ ፈቃድ የሚያበቃው፤

ሀ) የተሰጠው ፍቃድ መታደስ ባለበት ጊዜ ሳይታደስ ሲቀር ወይም ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎችን ባለሚሟላቱ ምክንያት የእድሳት ጥያቄው ተቀባይነት ሳያገኝ ሲቀር፤ ወይም

ለ) ፍቃዱን የወሰደው ስደተኛ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 20 ላይ በተገለጹት አስገዳጅ ሁኔታዎች ምክንያት ወደ መጠለያ ጣብያ ተመልሶ ለመኖር ጥያቄ ሲያቀርብ፤

ሐ) ስደተኛው በፈቃዱ ወደ መጠለያ ጣቢያው ለመመለስ ሲጠይቅነው።

2. በዚህ አንቅጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ

ሀ) ፍቃዱ በማጭበርበር ወይም በሕገ ወጥ መንገድ የተገኘ ከሆነ፣ ወይም

ለ) ስደተኛው በሕግ መሰረት ተደጋጋሚ ወንጀለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ፣ ወይም

ሐ) ለሚኖርበት አካባቢ የደህንነት ስጋት መሆኑን ተገቢው አካል ካረጋገጠ፣ ወይም

መ) በሰዎች ሕገ ወጥ ዝውውር ውስጥ ተሳታፊ በመሆኑ ምክንያት በወንጀል ከተቀጣ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የተሰጠው ፈቃድ ሊሰረዝ ይችላል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 ላይ በተመለከተው መልኩ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር የተሰጠው ፈቃድ የተሰረዘበት ስደተኛ ፍቃዱ እንዲሰረዝ ምክንያት የሆነው ሁኔታ አሳማኝ በሆነ መልኩ መቀየሩ ሲረጋገጥ በአዲስ መልኩ ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ ለመኖር ፍቃድ ሊሰጠው ይችላል።

4. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር የተሰጠ ፈቃድ በዚህ አንቅጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሰረት ሲያበቃ ወይም ሲሰረዝ ስደተኛው ወደ መጠለያ ጣብያ የሚመለስ ይሆናል።

## 20. ወደ መጠለያ ጣብያ ስለመመለስ

ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት የሚኖሩ ስደተኞች

1. ለመኖር የሚያስችላቸዉን የተሟላ ወጪ በመሸፈን ስፖንሰር የሆነው ሰው በራሱ ፍላጎት፣ በመጥፋት፣ በሞት፣ በህመም ወይም በሕግ ምክንያት ስፖንሰር ማድረጉን ካቋረጠ፤ ወይም

2. በሕጋዊ ሥራ ላይ መሰማራት የሚያስችላቸው የስራ ፈቃድ ሲሰረዝ ወይም በሕጋዊ ሥራ ላይ መሰማራት አዳጋች ሲሆን፤ ወይም

3. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት የመኖር ፈቃድ አግኝቶ እያኖረ የሚገኝ የቤተሰብ አባላቸው ወደ መጠለያ ጣብያ የተመለሰ ከሆነ ወደ መጠለያ ጣብያ የሚመለሱበትን ሁኔታ ኤጀንሲው ሊያመቻች ይችላል።

## 21. ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለሚኖሩ ስደተኞች ስለሚሰጥ ፕሮቴክሽን

ኤጀንሲው በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ከየተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ከፍተኛ ኮሚሽነር እና ሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመኖር ፍቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች ሕጋዊ ጥበቃ (ፕሮቴክሽን) እንዲያገኙ ያደርጋል፤

## 22. በከተማ ድጋፍ እያገኙ ስለመኖር

1. በዚህ ክፍል አንቀጽ 20 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ስደተኞች በከተማ ድጋፍ እያገኙ የሚኖሩ መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ መታወቂያ ይሰጣቸዋል።

2. በከተማ ድጋፍ እያገኙ የመኖር ሁኔታ የሚጀምርበት፣ የሚያበቃበት እና ሌሎች የአፈጻጸም ዝርዝር ጉዳዮች ኤጀንሲዉ እና አጋር የሰብአዊ እርዳታ ድርጅቶቸ በሚስማሙት የአሰራር ስነ ስርዐት መሰረት የሚተገበር ይሆናል፡፡

3.በከተማ ድጋፍ እያገኙ ለመኖር ዉሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጥያቄ የሚያቀርቡ ስደተኞች ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ በመደበኛነት ለመኖር የሚያስችሉ ሁኔታዎች አለመሟላታቸዉ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

4.ከመጠለያ ጣቢያ በዚህ መመሪያ ሌሎች ክፍሎች በተገለጸዉ መሰረት የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይዘዉ የሚወጡ ሲሆን በከተማ ድጋፍ እያገኙ የሚኖሩ ስደተኞች መሆናቸዉን የሚያረጋግጥ መታወቂያ በኤጀንሲዉ ዋናዉ መ/ቤት አማካኝነት ይሰጣቸዋል፡፡

**23. ስደተኞች በከተማ ድጋፍ እያገኙ ለመኖር የሚያስችል ፈቃድ ለማግኘት የሚያስችሉ ሁኔታዎችና መስፈርቶች**

1. ስደተኛ ከመሆናቸዉ በፊት፣ በስደት ወቅት ወይም በመጠለያ ጣቢያ ሲኖሩ ያጋጠማቸዉ የጤና ችግር ሲኖር እና በመጠለያ ጣቢያ ዉስጥ እና በሽታው በአካባቢው ባለ የህክምና ማዕከል መታከም የማይችል ሆኖ ወደ ከተማ እንዲተላለፍ ሲወሰን፣
2. በንዑስ አንቀጽ አንድ በተጠቀሰዉ ስደተኛ ጥያቄ አቅራቢነት ሌላ ስደተኛ በአስታማሚነት በከተማ ድጋፍ እያገኘ እንዲኖር ኤጀንሲዉ እዉቅና ሲሰጥ፤
3. ህይወትን አደጋ ላይ የሚጥል የፕሮቴክሽን ወይም የጸጥታና ደህንነት ስጋት ሲኖር እና በከተማ ድጋፍ እያገኙ መኖር የመጨረሻ መፍትሄ መሆኑ በኤጀንሲዉ ሲረጋገጥ፣
4. በመጠለያ ጣቢያ ዉስጥ መኖር ለስደተኛዉ ሁለንተናዊ ደህንነት ተግዳሮት እንደሚፈጥር ተረጋግጦ ሰብዐዊነትን ግምት ዉስጥ በማስገባት በአካል ጉዳት፣ በእርጅና እና በመሳሰሉ ምክንያቶች ህይወታቸዉ ለአደጋ የተጋለጠ ስደተኞች በከተማ ድጋፍ እያገኙ ኤጀንሲው ከአጋር ድርጅቶች ጋር በመነጋገር እንዲኖሩ ይፈቀዳል፡፡

## ክፍል አራት

## ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በጊዜያዊነት ስለመንቀሳቀስ

**24. የይለፍ ፍቃድ ስለመስጠት**

ማንኛውም ስደተኛ ከቦታ ቦታ መዘዋወር እንዲችል በየደረጃው ባሉ በስደተኞች ጣቢያዎች፣ በዞን ማስተባበሪያ ጽ/ቤትና በኤጀንሲው የሚዘጋጅ የይለፍ ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

## 25.የይለፍ ፍቃድ የማያስፈልግባቸው ሁኔታዎች

1. የጸጥታ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት የዞን የማስተባበሪያ ጽ/ቤት በሚለያቸው የስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ዙሪያ ባሉ አካባቢዎችና አቅራቢያ ከተሞች ስደተኞች ያለመንቀሳቀሻ ፈቃድ መዘዋወር እንዲችሉ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ወደ ክልል ከተሞች የሚሄዱ ስደተኞች የመንቀሳቀሻ ፈቃድ መያዝ አለባቸው፡፡

## 26. የይለፍ ፈቃድ በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ እና ማጣሪያ ጣቢያ ስለመስጠት

ማንኛውም ስደተኛ በሚከተሉት ሁኔታዎች በስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ወይም ማጣሪያ ጣቢያ ከቦታ ቦታ መዘዋወር እንዲችል የይለፍ ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

1. ድጋፍ እያገኙ በከተማ ስደተኝነት ለመቆየት፣ ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ውጭ በመደበኛነት ለመቆየት፣ ለውጭ ጉዞ ዝግጅት፣ የሙያ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት ኖሮትስራ ለመፈለግና መሰል ጉዳዩች ለማከናወን የአንድ አመት የይለፍ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ለቤተሰብ ጥየቃ፣ እረፍት፣ ጉብኝት፣ ለሐዘን፣ ጋብቻና ዘመድ ለመሸኘትና ለመሳሰሉ አጭር ቆይታዎች እንደሁኔታው እየታየ ለሦስት ወር የሚያገለግል የይለፍ ፍቃዱን ከሰጠው የመጠለያ ጣቢያ ወይም ማጣሪያ ጣቢያ ውጭ የማይታደስ የደርሶ መልስ ፍቃድ ይሰጣል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተጠቀሱ ምክንያቶች በዞን ፕሮግራም ማስተባበሪያ ፅ/ቤት የይለፍ ወረቀት ለማግኘት እንዲችል የደርሶ መልስ ፍቃድ ይሰጣል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) የተቀመጠው ቢኖርም ለውጭ ጉዞ ዝግጅትና ለከተማ ስደተኝነት ከመጠለያ ጣቢያዎች የሚሰጥ የይለፍ ፍቃድ የሚሰጠው ከአዲስ አበባ ስደተኞች አገልግሎት ቡድን ተጣርቶ ሲላክ ብቻ ነው፡፡

## 27. የይለፍ ፈቃድ በዞን ፕሮግራም ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ስለመስጠት

ማንኛውም ስደተኛ በሚከተሉት ሁኔታዎች በዞን ፕሮግራም ማስተባበሪያ ፅ/ቤት ከቦታ ቦታ መዘዋወር እንዲችል የይለፍ ወረቀት ሊሰጠው ይችላል፡፡

1. ለከፍተኛ ህክምና ወደ ተለያዩ የኢትዮጵያ ከተሞች በሚገኙ ሆስፒታሎች ለሚሄድ ስደተኛ ወይም ጥገኝነት ጠያዊ የይለፍ ወረቀት ይሰጣል፡፡
2. ለመንግስት የሥራ ጉዳይ ለሚፈለግ ስደተኛ የይለፍ ወረቀት ይሰጣል፡፡
3. ከአዲስ አበባ ወደ ዞን የሚላክ የፋክስ መልዕክትን መሰረት በማድረግ ከመጠለያ ጣቢያ ወይም ማጣሪያ ጣቢያ ስደተኛ እንዲመጣ ፋክስ ወይም ቴሌግራም ሊልክ ይችላል፡፡
4. በዞን ማስተባበሪያ ፅ/ቤት አቅራቢያ በከተማ ስደተኝነት ለሚኖር ስደተኛ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ከማጣሪያ ጣቢያ ወይም ከመጠለያ ጣቢያ ለተለያዩ ምክንያቶች ከድንበር አቅራቢያ ውጭ ፍቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 28. የይለፍ ፈቃድ በዋናው መስሪያ ቤት ስለሚሰጥበት ሁኔታ

ማንኛውም ስደተኛ በሚከተሉት ሁኔታዎች የይለፍ ፈቃድ በአዲስ አበባ/ማዕከል ሊሰጠው ይችላል፡፡

1. በተለያዩ ከተሞች በከተማ በስደተኝነት ፍቃድ ያገኘ፣ ወደ ውጭ ፕሮሰስ ለመሄድ የኢምባሲ ህጋዊ ዶክመንት ማስረጃ ላቀረበ፣ ለጋብቻ፣ የሙያ ወይም የከፍተኛ ትምህርት ዝግጅት ኖሮት ስራ ለመፈለግና ለመሳሰሉ ምክንያቶች እንደየአስፈላጊነቱ እስከ ሁለት ጊዜ ሊታደስ የሚችል የአንድ አመት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2. ለኢሚግሬሽን፣ ለጋብቻ፣ ለኤምባሲ፣ ለትምህርት፣ ለክፍለ ከተማ፣ ፤ለባንኮችና ለመሳሰሉት ተቋማት አገልግሎት ለማግኘት እንዲቻል እንደየአስፈላጊነቱ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3. ከአገር ውስጥም ይሁን ከውጭ አገር በተለያየ ምክንያቶች ከስደተኛ መጠለያ ጣቢያ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጡላቸው በአካል ቀርበው ለሚያመለክቱ ወይም የውጭ ጉዞ ዝግጅት/ፕሮሰስ ሰነድ ለሚያቀርቡ ባላጉዳዮች ሰነዱን በማጣራት እንዲመጣ የተጠየቀው ስደተኛ የይለፍ ፍቃድ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

4. የንብረት ጉዳይ ለመከታል የሚያመለክት ስደተኛ በጊዜያዊነት አዲስ አበባ መቆያ በፕሮቴክሽን ኦፊሰሮችና የስደተኞች አገልግሎት በጋራ ኮሚቴ ታይቶ በሚሰጥ ውሳኔ መሰረት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

5. በጸጥታና በጤና ችግር ምክንያት አዲሰ አበባ ላይ የስደተኝነት ዕውቅና አሰጣጥ ሂደት እንዲፈፀምለት ለሚያመለክት ጥገኝነት ጠያቂ ለአንድ አመት ጊዜያዊ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

6. ከተለያዩ አገራት ወደ አዲስ አበባ ለሚገቡ ጥገኝነት ጠያቂዎች ወደ ማጣሪያ ጣቢያ አስፈላጊውን ምዝገባ እንዲያደርጉ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ ይሰጣል፡፡ የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የቆይታ ጊዜ እንየማጣሪያ ጣቢያዎቹ ርቀቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

7. ስደተኞች ተገቢውን ማስረጃ በማቅረብ ወደ ሶስተኛ ሀገር በህጋዊ መንገድ ተሻግሮ ለመኖር፣ ከቤተሰብ ጋር ተቀላቅሎ ለመኖር፣ ለትምህርት እና ለህክምና አገልግሎት ለማግኘት ተገቢውን ሰነድ በማቅረብ መሄድ የሚችሉ ቢሆንም ከዚህ ውጭ ስደተኛው በራሱ ጥያቄ ሲያቀርብ ጥያቄው በፕሮቴክሽን ኦፊሰሮች የስደተኞች አገልግሎት ቡድን የጋራ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡

8. በህገ-ወጥ መንገድ ሲንቀሳቀስ በፖሊስ ተይዞ ለሚመጣ ስደተኛ ለምን እና እንዴት ለመንቀሳቀስ እንደቻለ ተጣርቶ ወደ መጠለያ ጣቢያው መመለሻ ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

9. በከተማ ስደተኝነት የሚኖር ስደተኛ በተለያየ ምክንያት ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ ፈቃድ ሲጠይቅ እሰከ ሦስት ወር የሚያገለግል የይለፍ ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

10. ከመጠለያ ጣቢያ ለዕረፍት የመጣ ስደተኛ የዕረፍት ፍቃዱ ቢጠናቀቅም የውጭ ጉዞ ፕሮሰስ እንዳለው ማስረጃ ካቀረበ ወደ ካምኘ የመሄጃ ጊዜው ከደረሰ በአዲስ አበባ እንዲቆይ የአንድ አመት ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

11. ያለይለፍ ፈቃድ ሲንቀሳቀስ የተገኘ ስደተኛ ወደ መጣበት የስደተኛ መጠለያ ጣቢያ መመለሻ ፈቃድ ብቻ ሊሰጠው ይችላል፡፡

**29.የይለፍ ፈቃድ መርሆዎች**

1. የይለፍ ፈቃድ የሚሰጠው ስደተኛው በፍላጎቱ ሲያመለክት ብቻ ነው፡፡

2. የይለፍ ፈቃድ የሚያገለግለው በተፈቀደው ቦታ ለመንቀሳቀስ፣ ፈቃዱ የተሰጠበትን ዓላማ ለማከናወን እና በተዛማጅነትም በእንቅስቃሴ ወቅት ለስደተኞች የሚሰጡ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡

## 30.የይለፍ ፈቃድ የተሰጣቸው ስደተኞ ችግዴታዎች

ማንኛውም የይለፍ ፈቃድ የተሰጠው ስደተኛ፤

1. በሕገ ወጥ ስራዎችና ለሕዝብ ሞራል ተፀራሪ በሆኑ ተግባራት ላይ ያለመሠማራትና የአገሪቱን ሕጎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡
2. የተጭበረበሩ ሰነዶችን ከመጠቀምና የተሰጠውን የይለፍ ፈቃድ ሌላ ሰው እንዲጠቀምበት ከማድረግ መቆጠብ አለበት፡፡
3. ለመንቀሳቀስ ከተፈቀደበት ቦታ ውጭ ያለፈቃድ መንቀሳቀስ የለበትም፡፡

## 31.የይለፍ ፈቃድ ይዘት

ለስደተኞች በማንኛውም ደረጃ በኤጀንሲው የሚሰጥ የይለፍ ፈቃድ የሚከተለው ይዘት ይኖረዋል፡፡

1. የስደተኛው ስም ከነአያት፤
2. የመኖሪያ ቦታ ወይም የስደተኛ መጠለያ ጣቢያ፤
3. የስደተኛው የግል መለያ ቁጥር፤
4. ፈቃዱ የተሰጠበት ቀን፤
5. ፈቃዱ የሚያልቅበት ጊዜ፤
6. ፈቃዱ የተሰጠበት መዝገብ ቁጥር፤
7. ስልክ ቁጥር፤
8. ለመንቀሳቀስ የተፈቀደበት ቦታ፤
9. ፈቃዱ የተሰጠበት ምክንያት፤
10. አብሮ የሚጓዝ የቤተሰብ አባል ዝርዝር፤
11. ፈቃዱ የተሰጣቸው የቤተሰብ አባላት ጉርድ ፎቶግራፍ፤
12. በአደጋ ጊዜ ተጠሪ ስምና አድራሻ፤
13. ፈቃዱ የተሰጠው ስደተኛ የሚቆይበት ቦታ ሙሉ አድራሻ፤

14.የመንቀሳቀሻ ወረቀቱ በኮምፒውተር መፃፍ አለበት፡፡

**32.የይለፍ ፈቃድ እድሳት**

በዚህ መመሪያ መሰረት የይለፍ ፈቃድ የሰጠ የኤጀንሲው አካል የይለፍ ፈቃዱን እንደየአስፈላጊነቱ ሊያድስ ይችላል፡፡

**33.የይለፍ ፈቃድን ስለመተካት**

1. የይለፍ ፈቃዱ የጠፋ መሆኑን የፖሊስ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፣
2. የጠፋን ወይም የተበላሸን የማለፊያ ፍቃድ ለመተካት ማመልከቻ ማቅረብ የሚችለው ፍቃዱን ያገኘው ስደተኛ ወይም የቤተሰቡ አባል አማካኝነት ብቻ ነው፡፡
3. የይለፍ ፈቃዱ የተበላሸ ከሆነ የተበላሸው ፈቃድ ቅሪት ለኤጀንሲው ገቢ መደረግ ይኖርበታል፡፡
4. የመኖሪያ ፍቃድ ምትክ የተሰጠው ስደተኛ የጠፋውን ካገኘው ወይም የሚገኝበትን ካወቀ ወድያውኑ ለኤጀንሲው መመለስ ወይም ያለበትን ማሳወቅ አለበት፡፡

**34.የመንቀሳቀሻ ፈቃድ የሚያበቃበት ሁኔታዎች**

የይለፍ ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያበቃ ይችላል፤

1. የይለፍ ፍቃዱ የተሰጠው ስደተኛ በራሱ ፈቃድ ወደ መጣበት መጠለያ ጣቢያ ወይም መኖሪያ ቦታ ሲመልስ፤
2. ስደተኛው በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ላይ የተቀመጡ ግዴታዎችን መተላለፉ ከተረጋገጠ፤
3. የስደተኝነት ዕውቅናውን ያጣ ከሆነ፤
4. ስደተኛው ከአገር መውጣቱ ከተረጋገጠ፤
5. የይለፍ ፈቃዱ በሀሰተኛ ማስረጃ፣ በማታለል፣ በማጭበርበር፣ ወይም ሌላ ሕገ-ወጥ መንገድ የተሰጠው መሆኑ ከተረጋገጠ፤
6. የመኖሪያ ፍቃዱ ጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኂላና ሳይታደስ ከቀረ፤

7. ስደተኛው ፈቃዱን ይዞ መቆየቱ ለሀገር ጥቅምና ደህንነት ተገቢ አለመሆኑ በኤጀንሲው ሲታመን፡፡

**35.መረጃ መያዝና ማደራጀት**

1. ኤጀንሲው ስደተኞችና የተሰጡ የይለፍ ፈቃዶች በተመለከተ ጠቅላላ መረጃ ይይዛል፣ ያደራጃል እንዲሁም እንደየአስፈላጊነቱ ለሚመለከተው አካል መረጃ ይሰጣል፡፡

2. በሁሉም ደረጃዎችየይለፍ ፈቃድ የተሰጣቸው ስደተኞች ስም፣ ፈቃዱ የተሰጠበትና የሚቆይበት ጊዜና የፈቃዱ ዓላማ በስደተኞች የመረጃ ቋት ውስጥ ተመዝግቦ ይያዛል፡፡

**36. ይግባኝ**

ማንኛውም ስደተኛ የይለፍ ፈቃድ ለማውጣት አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ፍቃዱን ለማግኘት ከተከለከለ ፍቃዱን ለከለከለው የስደተኞች መስተንግዶ ሰራተኛ የበላይ አላፊ ይግባኝ የማለት መብት አለው፡፡

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**37. ለስደተኞች ስለሚደረግ ክትትልና ጥበቃ**

1. በዚህ መመሪያ መሰረት ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ እንዲንቀሳቀሱ ወይም እንዲኖሩ የተፈቀደላቸው ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎችን በተመለከተ የስደተኞች ጉዳይ አዋጅ፣ደንብና መመሪያዎች መተግበራቸውን ለማረጋገጥ ኤጀንሲው ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

2. ኤጀንሲዉ ከመጠለያ ጣቢያ ዉጪ የሚኖሩ ስደተኞች ተገቢዉን ጥበቃ እና ድጋፍ እንዲያገኙ ክትትል ያደርጋል፡፡ ለዚህ ተግባር የስደተኞች መብት ጥበቃ እና ድጋፍ ከሚመለከታቸዉ በተለያየ እርከን የሚገኙ የመንግስት አካላትና ሌሎች አጋር ድርጅቶችጋር በመተባበር ይሰራል፡፡

## 38. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. ከዚህ ቀደም በሥራ ላይ የነበሩ የስደተኞችን ከመጠለያ ጣቢያ ውጭ መንቀሳቀስ ወይም መኖር በተመለከተ የወጡ መመሪያዎች ወይም የውስጥ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ተተክተዋል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ከዚህ መመሪያ መውጣት በፊት የተሰጡ የይለፍ ፣ የከተማ ስደተኝነት እንዲሁም ከካምፕ ውጭ ለመኖር የተሰጡ ፈቃዶች ፀንተው ይቆያሉ፡፡

## 39. ስለአገልግሎት ክፍያ

ስደተኞች ወይም ጥገኝነት ጠያቂዎች በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ማንኛውንም አገልግሎቶች ለማግኘት የአገልግሎት ክፍያ አይከፍሉም፡፡

## 40. ሰለ ተሻሩ ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚጋጩ የትኛውም መመሪያ ውስጥ የተደነገጉት በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

## 41. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከታህሳስ 20/2012 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ታህሳስ 20/2012 ዓ.ም*


*አዲስ አባባ*

*አበደ ጫኔ*

*በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ*

*የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ*

*ዋና ዳይሬክተር*



D/Director General (Refugees)
Protection Directorate Director
Urban/ OCP Protection Team Leader
Protection Staff A (covers Addis and the ff)
Protection Staff B (covers Addis, Borena, South Omo and the ff)
Shire Zonal Protection Team Leader (Covers Tigray)
Gambella Zonal Protection Team Leader (Covers Gambella)
Assosa Zonal Protection Team Leader (Covers Benishangul Gumuz)
Melkadida Zonal Protection Team Leader (Covers Liben Zone and the Surrounding
Jijiga Zonal Protection Team Leader (Covers Jjijiga and the Surrounding)
Protection Staff A (Covers Shire and the surrounding)
Protection Staff B (Covers Shire and the surrounding)
Mekelle Protection Team (Covers Mekelle and Afar)
Protection Staff A
Protection Staff B
Protection Staff A
Protection Staff B
Protection Staff A
Protection Staff B
Protection Staff A
Protection Staff B